STAY SAFE MN



# የ Johnson & Johnson የኮቪድ-19 ክትባት ለአፍታ መቆም፡- ማወቅ የሚገባዎት

የ Johnson & Johnson የኮቪድ-19 ክትባት ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የሚመከር ነው። ከኮቪድ-19 ለመጠበቅ መውሰድ የሚያስፈልግዎት የ Johnson & Johnson ክትባት መጠን አንድ ብቻ ነው።

## ለአፍታ ስለማቆም

የ Johnson & Johnson ክትባት የደም መርጋት ጉዳይን እንዴት ማወቅ እና ማከም እንደሚቻል ለማወቅ ከመጠቀም ለአፍታ ቆሞ ነበር። በቆመበት ወቅት፣ የህክምና ባለሙያዎች የክትባት ውሂቦችን ገምግመው የዚህ ክትባት ጥቅሞች በጣም አነስተኛ ከሆነ አደጋው እንደሚያመዝኑ አረጋግጠዋል። የደም መርጋት ጉዳይ ሊታከም የሚችል ነው፤ ግን ሐኪሞች እንዴት እንደሚለዩት፣ እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉ እና እንዴት እንደሚያክሙ ማወቅ አለባቸው።

## በ Johnson & Johnson ክትባት መከተብ

- ሴቶች፣ በተለይም ከ 50 ዓመት በታች ያሉ፣ በደም መርጋት ጉዳይ ሊከሰቱ የሚችሉ ምልክቶችን መገንዘባቸው አስፈላጊ ነው። ክትባትዎን ከወሰዱ በኋላ ለሦስት ሳምንታት ያህል፣ የሚከተሉትን ያትኩሩ፡-

- የትንፋሽ እጥረት
- የደረት ህመም
- የእግር እብጠት
- የማይለቅ የሆድ/የጨጓራ ህመም
- ከባድ ራስ ምታት ወይም የማይለቅ ራስ ምታት
- የእይታ መደብዘዝ
- በቀላሉ መዘጎን ወይም መርፌው ከተሰጠበት ቦታ ባሻገር በቆዳው ስር ጥቃቅን የደም ጠብታዎች

- እነዚህ ምልክቶች ከታዩብዎት፣ ወደ ድንገተኛ ክፍል ሕክምና ወይም ወደ አስቸኳይ እንክብካቤ ይሂዱ። በቅርቡ የ Johnson & Johnson ክትባት እንደወሰዱ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢው ይንገሩ።
- እነዚህ ምልክቶች ለመታየት ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስዱ ሲሆን ክትባት ከወሰዱ በኋላ ከአንድ እስከ ሁለት ቀናት ውስጥ ከሚከሰቱ እና ለጥቂት ቀናት ብቻ ከሚቆዩ ከተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች የበለጠ ከባድ ናቸው ።

**የ Johnson & Johnson ክትባት ከአንድ ወር በላይ በፊት ከወሰዱ እነዚህን ሁኔታዎች የመታየት ዕድልዎ አናሳ ነው።**

## እያንዳንዱ ማህበረሰብ ሁሉንም የኮቪድ-19 ክትባቶች ማግኘት ይችላል

ሁሉም የሚኒሶታ ነዋሪዎች የፈለጉትን ክትባት የመውሰድ ምርጫ አላቸው።

ሁሉም ህብረተሰብ በብዙ የተለያዩ የክትባት ጣቢያዎች ሶስቱን ክትባቶች ማግኘት ይችላል። ሁልጊዜ በክትባት ክሊኒክ ውስጥ የትኛው የክትባት ምርት እንደሚሰጥ በኦንላይን ማየት ወይም መደወል እና መጠየቅ ይችላሉ።

# አደጋዎች እና ጥቅሞች

**የ Johnson & Johnson ክትባት ጥቅሞች ከትንሽ አደጋው ያመዝናሉ።**

**አደጋ፡-** ሴቶች፣ በተለይም ከ 50 ዓመት በታች ያሉ፣ በደም መርጋት ጉዳይ ሊከሰቱ የሚችሉ ምልክቶችን መገንዘብ አለባቸው። ይህ አደጋ 50 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች እና በሁሉም ዕድሜ ውስጥ ላሉ ወንዶች በጣም አናሳ ነው።

**ጥቅሞች፡-** የ Johnson & Johnson ክትባት ከባድ በሽታን፣ በሆስፒታል መተኛትን እና በኮቪድ-19 መሞትን በመከላከል በጣም ጥሩ ነው። ለሙሉ መከላከል የሚያስፈልገው አንድ የክትባት መጠን ብቻ ነው። የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለማቆም የሚረዳ አስፈላጊ መሣሪያ ነው።

## የክትባት ደህንነት

የኮቪድ-19 ክትባቶች፣ Johnson & Johnson ን ጨምሮ፣ ተጨማሪ ገንዘብ እና ሀብቶች እንዲሁም ቀደምት ምርምር በመደረጉ በፍጥነት ተሰርተዋል። ደህንነትን ለመፈተሽ የሚደረጉ እርምጃዎች እንዳልተዘለሉ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ደህንነታቸው የተጠበቀ የኮቪድ-19 ክትባቶችን ማግኘት ዋነኛው ጉዳይ ነው። የሕክምና ተመራማሪዎች ክትባቶቹ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከመፈቀዳቸው በፊት ደህንነታቸው የተጠበቀ እና የሚሰሩ መሆናቸውን የክትባት ጥናት መረጃዎች እንደሚያሳዩ ማረጋገጥ ነበረባቸው።

- የጤና ባለሥልጣናት በምግብ እና መድኃኒቶች አስተዳደር ከተፈቀዱ በኋላ ሁሉንም የኮቪድ-19 ክትባቶች ደህንነት ለመቆጣጠር በርካታ የተለያዩ ስርዓቶችን ይጠቀማሉ።
- እነዚህ ስርዓቶች በክሊኒካዊ ሙከራዎች ወቅት ያልተገኙ በጣም ጥቂት የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉ መለየት ይችላሉ።
- ባለሙያዎች ማንኛውንም የደህንነት ስጋት ወዲያውኑ ይገመግማሉ እንዲሁም ያሳውቃሉ።

ሰዎች እድሉን ሲያገኙ እንዲከተቡ እንመክራለን። ሁሉም የኮቪድ-19 ክትባቶች የኮቪድ-19 በሽታን በተለይም ከባድ ህመምን እና ሞትን ለመከላከል  እንደምረዱ ኤክስፐርቶች ይስማማሉ



## ጥያቄዎች?

በክትባት ላይ ስላልዎት ጥያቄዎች ሊያደርጉ የሚችሉት የተሻለ ነገር፣ ከዋና ተንከባካብ ሐኪምዎ ወይም ከሌላ የጤና አገልግሎት ሰጪዎ ጋር መነጋገር ነው። እነሱ መረጃን ማጋራት እና ያንን መረጃ ከራስዎ ሕይወት እና ሁኔታዎች አውድ ውስጥ እንዲያስገቡ ይረዱዎታል። የ Johnson & Johnson ክትባት ለእርስዎ የማይመረጥ ከሆነ፣ የደም መርጋት አደጋ ያልታየባቸው ሌሎች የኮቪድ-19 የክትባት አማራጮች አሉ።

MINNESOTA

mn.gov/vaccine

Minnesota Department of Health | health.mn.gov | 651-201-5000 | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975

አማራጭ ቅርጸት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.us ን ያነጋግሩ። (Amharic)

5/28/2021